# የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

# የምግብ ጨው ቁጥጥር

# መመሪያ

ነሐሴ 2004 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ.................................................................................................1

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርእስ....................................................................................2
2. ትርጓሜ..........................................................................................2
3. ዓላማ............................................................................................2
4. የተፈፃሚነት ወሰን............................................................................2

ክፍል ሁለት

ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

5. ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት.................................3
6. ስለ ነጥብ አሰጣጥ ሂደት...................................................................3
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማያሰጡ ሁኔታዎች..........................4
8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ ማይጠየቅባቸው ሁኔታዎች...........5
9. የአድራሻ ለውጥ ስለማድረግ..............................................................5
10.ምትክ ስለ ማግኘት..........................................................................5
11.ስለ እድሳት....................................................................................5
12.የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ.......................................6

ክፍል ሦስት

ስለ ማምረቻና ማከማቻ ህንፃ አሰራርና አስፈላጊ መሳሪያዎች

13.ስለ ህንፃ አሰራር ሁኔታ.....................................................................6
2. ስለ ማከማቻ ህንፃ............................................................................7

ክፍል አራት

ስለ ቴክኒካል ባለሞያዎች፣ ጤንነትና ሞያ

15.ስለ ቴክኒካል ባለሞያ.......................................................................10
16.ስለ ሰራተኞች ጤናና ንፅህና አጠባበቅ ሁኔታ........................................10
17.የቴክኒካል ባለሞያ ሃላፊነት...............................................................11

ክፍል አምስት

የምግብ ጨው ስለ ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክና ጅምላ ማከፋፈል

18.የምግብ ጨው ስለማምረት................................................................12
19.ስለ ጨው ማበልፀግያ ውህዶች..........................................................12

20.ስለ የአዮዲን መጠንና በካይ ነገሮች ........................................................................ 13
21.የምግብ ጨው ስለ ማሸግ .................................................................................. 13
22.ስለ ገላጭ ፅሁፍ ............................................................................................. 13
23.የምግብ ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ሰለማስገባት .......................................................... 14
24.የምግብ ጨው ወደ ውጭ ሀገር ስለ መላክ .............................................................. 15
25.የምግብ ጨው ስለ ማከፋፈል .............................................................................. 15
26.የምግብ ጨው ስለ ማከማቸት .............................................................................. 16
27.የምግብ ጨው ስለ ማጓጓዝ ................................................................................ 16
28.አዮዲን የሌለው ጨው በጥቅም ላይ ስለማዋል .......................................................... 16

## ክፍል ስድስት

## አስተዳዳራዊ እርምጃዎች

29.ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት .................................................................................. 17
30.ስለ እገዳ .................................................................................................... 17
31.ስለ ስረዛ .................................................................................................... 18
32.የምግብ ጨውን ሰለ መያዝ ................................................................................ 19
33.የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ መመለስ ...................................................... 20
34.እገዳና ስረዛ ስለማንሳት ................................................................................... 20
35.የምግብ ጨው ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ .............................................................. 20
36.የምግብ ጨው ከገበያ ላይ ስለ መሰብሰብ /Product recall/ ........................................... 20
37. የተበላሸ ወይም ተፈላጊውን ደረጃ ስለ ማያሟላ የምግብ ጨው .......................................... 21
38. አስተዳዳራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ .................................................. 21

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

39.መረጃ ስለ መያዝ ........................................................................................... 22
40. የምግብ ጨው ስለ ማስተወወቅ ........................................................................... 22
41. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ ......................................................................... 22
42.ስለ አገልግሎት ክፍያ ....................................................................................... 23
43.የመተባበር ግዴታ ............................................................................................ 23
44.ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች ................................................................... 23
45.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ................................................................................. 23
*እዝሎች ---------------------------------------------------------------------------------------23-28*

## መግቢያ

ከዚህ ቀደም በሀገራችን ለምግብነት የሚቀርበው ጨው አዮዲን የሌለው በመሆኑ ይህም ህብረተሰቡን ለተለያዩ የጤና ችግሮች ስለሚያጋልጥ ጨው በአዮዲን እንዲበለፅግ በማስፈለጉ ፤

ማንኛውም በምግብ ጨው አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ንግድ ሥራ ላይ የሚሰማራ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የምግብ ጨው የሀገሪቱን የምግብ ጨው ደረጃ ያሟላ፣ ጥራትና ደህንነት የተጠበቀ ስለ መሆኑ ማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ፤

በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 55 (3) እና ደንብ ቁጥር 204/2003 አንቀፅ (10) መሰረት ይህ የምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 5/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በአዋጁና ደንቡ ላይ የተቀመጡት ትርጉሞች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ:

1) "የምግብ ጨው" ወይም "አዮዲን ያለው ጨው" ማለት ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዲሆን አግባብ ባለው አካል በሚወስነው መመዘኛ መሰረት ጨው ከአዮዲን በመደባለቅ የተዘጋጀ ጨው ነው፤

2) "አዮዲን የሌለው ጨው" ማለት ለሰው ምግብነት አገልግሎት የማይውሉ ምርቶችን ለማዘጋጀት ወይም ለማምረት የሚያገለግል ጨው ነው፤

3) "ድርጅት" ማለት በምግብ ጨው ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክ ወይም ጅምላ ማከፋፈል ስራ ላይ የተሰማራ ተቋም ነው፤

4) "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

5) "አዋጅ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው፤

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በምግብ ጨው ማምረት፣ መላክ፣ ማስመጣትና ጅምላ ማከፋፈል ስራ ላይ የሚሰማሩና የተሰማሩ ድርጅቶች የሚያቀርቡት የምግብ ጨው ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥና ተፈላጊው የአዮዲን መጠን እንዲኖረው በማድረግ በጥራት ጉድለትና ከአዮዲን እጥረት ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችል የጤና ችግር ለመከላከል ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላው ሀገሪቱ በምግብ ጨው ማምረት፣ መላክ፣ ማስመጣትና ጅምላ ማከፋፈል ስራ ላይ በተሰማሩና በሚሰማሩ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

### 5. ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

1) ማንኛውም ሰዉ ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ በምግብ ጨው መላክ ፣ማስመጣት ወይም ማከፋፈል ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡
2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው በክፍል ሶስትና አራት ስር የተጠቀሱትን አስፈላጊ መስፈርቶች ካሟላ በኋላ በእዝል አንድ ስር ከሚገኘው ማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
3) ማመልከቻዉ የተሟላ ከሆነ ባለሥልጣኑ ከሁለት አባላት ባላነሰ የተቆጣጣሪ ቡድን ድርጅቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለክፍያ እንዲታይ ያደርጋል፡፡
4) ድርጅቱ አስፈላጊውን መሥፈርት ማሟላቱ ከተረጋገጠና የአገልግሎት ክፍያ ከከፈለ በኃላ ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ መስጠት አለበት፡፡
5) በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የኢንስፔክሽን ሪፖርቱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ (6) ላይ የተዘረዘሩት መሰረታዊ ሁኔታዎች ከተጓደሉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አይሰጥም፡፡ ሆኖም ድርጅቱ ማሟላት ያለበትን ሁኔታዎች እንዲያሟላ በፅሁፍ ተነግሮት ካሟላና ተገቢዉን ክፍያ ከከፈለ በድጋሚ ሊታይለት ይችላል፡፡

### 6. ስለ ነጥብ አሰጣጥ ሂደት

1) የዚህ መመሪያ አንቀፅ (6) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ቢያንስ 60% ማሟላት አለበት፡፡
2) ድርጅቱ በኢንስፔክሽን ወቅት ለሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ መሰረት እንዲያሟላ ከባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች ጋር በእዝል 3 ላይ የተቀመጠውን የመተማመኛ ስምምነት ሰነድ መሰረት የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡
3) ድርጅቱ በገባው የመተማመኛ ስምምነት ሰነድ መሰረት ክፍተቶቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ካልተሟሉ እንደአግባቡ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተደነገጉ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማያሰጡ ሁኔታዎች

1) ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች ድርጅት በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሁኖ ከሚከተሉት መስፈርቶች ውስጥ አንዱን ካላሟላ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ አይሰጠውም፤

   ሀ) የጥሬ እቃና ምርት ማከማቻ፣ የጨው ማምረቻና የጨው ማበልፀጊያ ውህዶች ማከማቻ ካልተሟሉ፣

   ለ) የማምረቻና ማከማቻ ህንፃው ወለልና ግድግዳ ለማፅዳት ምቹ ካልሆነ፣

   ሐ) ጨው ለማምረትና አዮዳይዝድ ለማድረግ የሚያስችሉ ማሽነሪዎችና የጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪ መሳሪያዎች ካልተሟሉ፣

   መ) እንደአከባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም ኤር ኮንዲሽነር ካለተሟላ፣

   ሠ) የተቀመጡ ቴክኒካል ባለሞያዎች ካልተሟሉ

2) ማንኛውም የምግብ ጨው አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቀ ሁኖ ከሚከተሉት መስፈርቶች ውስጥ አንዱን ካላሟላ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አይሰጠውም፡፡

   ሀ) የምግብ ጨው ማከማቻ ከሌለ፤

   ለ) የማከማቻ ህንፃው ግድግዳና ወለል ለማፅዳት ምቹ ካልሆነ፤

   ሐ) የማከማቻ ክፍሉ በቂ የብርሃንና የአየር ዝውውር ከሌለው፤

   መ) እንደ አካባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር ካልተሟላ

   ረ) የተቀመጠው ቴክኒካል ባለሞያ ካልተሟላ

## 8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ ማይጠየቅባቸው ሁኔታዎች

ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያስፈልግ የምግብ ጨው ወደ አገር ዉስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ዉጭ ለመላክ የሚቻለዉ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል፡፡

1) ለግለሰብ ጠቀሜታ የሚውል ፤
2) ለሳይንሳዊ ምርምር አገልገሎት፤
3) ለሰብዓዊ እርዳታ አገልግሎት፤

## 9. የአድራሻና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ቀምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር ወይም የባለቤትነት ለውጥ ማድረግ የተከለከለ ነው።

## 10. ምትክ ስለ ማግኘት

ድርጅቱ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ከሆነ ምትክ ሊያገኝ የሚችለው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሲያሟላ ይሆናል፡፡

1) ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸበት ከሆነ የተበላሸዉን የምስክር ወረቀት ሲመልስ፤
2) ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ የጠፋበት ስለመሆኑ የሚገልፅ ከፍትህ አካል ማረጋገጫ ሲያቀርብ እና
3) አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል ነው፡፡

## 11. ስለ እድሳት

1) ማንኛዉም ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊታደሰለት የሚችለዉ የምስክር ወረቀቱ ካልታገደ፣ ካልተሰረዘ ወይም ድርጅቱ በራሱ ፈቃድ ስራዉን

ካላቋረጠ በየዓመቱ ከሐምሌ እስከ ነሐሴ ባሉ ሁለት ተከታታይ ወራት ብቻ ይሆናል፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የሚታደሰው አስፈላጊ መመዘኛዎች መሟላታቸው በባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች በዓመታዊ ኢንስፔክሽን ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

3) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀፅ (1) በተቀመጠው ገደብ የምስክር ወረቀቱ ካልታደሰ በየወሩ 50% ተጨማሪ ቅጣት በመክፈል ለሚቀጥሉት 2 ወራት ማሳዳስ ይችላል፡፡

4) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ሳይታደስ ከቀረ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

## 12. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ

ማንኛውም ድርጅት የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ ሁልጊዜ በግልፅ እና በሚታይ ቦታ ማሰቀመጥ አለበት፡፡

# ክፍል ሦስት

# ስለ ማምረቻና ማከማቻ ህንፃ አሰራርና አስፈላጊ መሳሪያዎች

## 13. ስለ ህንፃ አሰራር ሁኔታ

ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች ድርጅት የምግብ ጨዉን ለማምረት የሚውለው ህንፃ የሚከተሉት መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፤

### 1) ስለ ማምረቻ ህንፃ

ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች ድርጅት፤

ሀ) ማምረቻ ድርጅቱ የሚቋቋምበት አካባቢ ለምግብ ጨው ማምረት አገልግሎት ምቹ በሆነ ቦታ፣ የምግብ ጨው ሊበክሉ ለሚችሉ ነገሮች ተጋላጭ ያልሆነና የመሰረተ ልማት አውታሮች የተሟላለት መሆን አለበት፡፡

ለ) የህንፃው አሰራር የሚመረተውን የምግብ ጨው ለብክለት የማያጋልጥና በምርቱ ጥራት ላይ ተፅእኖ በማያሳድር መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፡፡

ሐ) ህንፃው የተገነባበት ግብአት ከድንጋይ፣ ብሎኬት፣ ሸክላ ወይም ሌሎች ሙቀት አምቀው ከሚይዙና በክፍሉ ሙቀት ላይ ተፅእኖ ከማያሳድሩ ቁሳቁስ የተገነባ መሆን አለበት፡፡

መ) የህንፃው ስፋት እንደሚያመርተው መጠን በቂ ሆኖ ቢያንስ የጥሬ እቃ፣ ምርትና የማበልፀጊያ ውሁዶች ማከማቻ፣ ማምረቻ፣ የጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ፣ ጥቅም ላይ የማይውል ጨው ማቆያ ቦታ፣ መፀዳጃ ቤት፣ የእጅ መታጠቢያና ሻወር ቤት ሊኖረው ይገባል፡፡

ረ) ግድግዳው በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ሰ) ወለሉ በሲሚንቶ ኮንክሪት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ የማያዳልጥ፣ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ውሀ የማያቁር መሆን አለበት፡፡

ሸ) የህንፃው በርና መስኮት የምግብ ጨዉን ሊበክሉ ከሚችሉ አቧራ፣ ዝናብ፣ ቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃንና ሌሎች በካይ ነገሮችን የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

ቀ) የክፍሉ ጣሪያ ሙቀት ሊቀንስ ከሚችል ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ ቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃንና ዝናብ የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

በ) ክፍሉ በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር ሊኖረው ይገባል፡፡

## 2) ስለ ማከማቻ ህንፃ

ማንኛውም የምግብ ጨው ለማከማቸት የሚውል ህንፃ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፤

ሀ) ህንፃው የሚከማቸውን የምግብ ጨው ለብክለትና ለአዮዲን ብክነት የማያጋልጥና በጥራቱ ላይ ተፅእኖ በማያሳድር መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤

ለ) ህንፃው የተገነባበት ግብአት ከድንጋይ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላ ወይም ሌሎች በክፍሉ ሙቀት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ ከማይችሉ ነገሮች የተሰራ መሆን አለበት፤

ሐ) የህንፃው ስፋት እንደሚያከማቸው የምግብ ጨው መጠን በቂ ሆኖ ቢያንስ የማከማቻ ክፍል እና ጥቅም ላይ የማይውል ጨው ማቆያ የተከለለ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤

መ) የህንፃው በርና መስኮት ነፍሳት፣ ቆርጣሚ እንስሳትና ሌሎች ጨዉን ሊበክሉ ከሚችሉ በካይ ነገሮች በማያስገባ መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤

ሠ) የህንፃው ወለል በሲሚንቶ ኮንክሪት፣ ሴራሚክ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ በቀላሉ ሊታጠብ የሚችልና ውሀ በማያቁር መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፤

ረ) የህንፃው ግድግዳ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ልሙጥ መሆን አለበት፤

ሰ) የክፍሉ ጣሪያ ሙቀት ሊቀንስ ከሚችል ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃንና ዝናብ የማያስገባ መሆን አለበት፤

ሸ) በቂ ብርሀንና የአየር ዝውውር ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 14. ስለ አስፈላጊ መሳሪያዎችና ግብአቶች

### 1) የምግብ ጨው ማምረቻ ድርጅት

ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች ድርጅት ጨዉን ለማምረት የሚያስፈልጉ የሚከተሉት መሳሪያዎችና ግብአቶች ሊኖረው ይገባል፤

ሀ) ድርጅቱ ጨዉን አዮዳይዝድ ለማድረግ የሚያስችሉ ቢያንስ የጨው ማጣሪያ፣ አዮዳይዝድ ማድረጊያ፣ የማበልፀጊያ ውህዶች ማደባለቂያ፣ ማሸጊያና የጥራት ምርመራ ለመካሄድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ሊኖሩት ይገባል፤

ለ) ከምርት ሂደቱ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ማናቸውም መሳሪያዎችና ማሽኖች ከዝገት የፀዱና ከስቴንለስ ስቲል ወይም ጨዉን ከማይበክል ማቴሪያል /food grade/ የተሰሩ መሆን አለባቸው፤

ሐ) እንደአከባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር ሊኖረው ይገባል፤

መ) ጨዉን የተመረተበት፣ የመጠቀሚያ ጊዜና የምርት መለያ ቁጥር ለማተም ወይም ለመፃፍ የሚያስችል መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

ሰ) ድርጅቱ ጨዉን ለማምረት የሚያስፈልጉ የአመራረት ሂደት ፍሰት፣ ጨዉ በአዮዲን የማበልፀግ ሂደት፣ የጨዉ ጥራት ላቦራቶሪ ቁጥጥር ስርዓት፣ የማሽነሪዎች ፅዳትና ንፅህና አጠባበቅ አሰራር ሂደት የሚያሳዩ ማንዋሎች ሊኖሩት ይገባል፤

ረ) የሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ እንደ ጋዎን፣ ጓንት፣ ማስክ፣ ቱታና ጫማ የመሳሰሉት ሊኖረው ይገባል፤

በ) በድርጅቱ ውስጥ ለሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች ለማከም የሚያስችል የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

ተ) ድርጅቱ የድንገተኛ እሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

ቸ) የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሊኖረው ይገባል፡፡

## 2) የምግብ ጨው ላኪ፣ አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት

ማንኛውም የምግብ ጨው አከፋፋይ ድርጅት ጨዉን ለማከማቸት የሚያስፈልጉ የሚከተሉት ግብአቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡

ሀ) እንደአከባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር፣

ለ) ለድንገተኛ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳርያ፣

ሐ) የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ፣

መ) እንደየስራ ባህሪው የሰራተኞች የግል ደህንነት መጠበቂያ ማቴሪያሎች፤

## ክፍል አራት

## ስለ ቴክኒካል ባለሞያዎች፣ ጤንነት እና ሞያ

### 15. ስለ ቴክኒካል ባለሞያ

1) በማንኛውም የምግብ ጨው ማምረቻ ድርጅት ውስጥ የምርት ክፍል ሀላፊ ሆኖ የሚሰራ ባለሞያ በምግብ ሳይንስና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ሳይንስና ኑትሪሽን፣ በምግብ ሀይጅን፣ በምግብ ኢንጅነሪንግ፣ በአፕላይድ ኬሚስትሪ፣ በኢንዳስትሪያል ኬሚስትሪ፣ በአፕላይድ ባዮሎጂ ወይም ከነዚህ ሞያዎች ተመሳሳይ በሆኑ ሞያዎች የተመረቀ ሁኖ ለዲፕሎማ 2 ዓመት፣ ለዲግሪ ዜሮ ዓመት ወይም ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
2) ማንኛውም የምግበ ጨው ማምረቻ በድርጅቱ ውስጥ የጥራት ቁጥጥር ክፍል ሀላፊ ሆኖ የሚሰራ ባለሞያ በምግብ ሳይንስና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ሳይንስና ኑትሪሽን፣ በአፕላይድ ኬሚስትሪ፣ በኢንዳስትሪያል ኬሚስትሪ፣ በአፕላይድ ባዮሎጂ፣ ኢንዳስትሪያል ላቦራቶሪ ቴክኒሽያን ወይም ከዚህ ሞያ ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ሞያዎች የተመረቀ ሁኖ ለዲፕሎማ 2 ዓመት፣ ለዲግሪ ዜሮ ዓመት ወይም ከዛ በላይ በምግብ ጥራት ቁጥጥር ስራ ተዛማጅ የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
3) ማንኛውም አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅትን በቴክኒካል ሀላፊነት የሚመራ ባለሞያ ቢያንስ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ 10ኛ ክፍል ወይም በድሮው የትምህርት ፖሊሲ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡
4) ቴክኒካል ባለሞያው ስለ አዮዲን ያለው ጨው አመራረት፣ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አከመቻቸትና አጠባበቅ ሁኔታና አሰራር እውቀት ቢኖረው ይመረጣል፡፡

### 16. ስለ ሰራተኞች ጤናና ንፅህና አጠባበቅ ሁኔታ

1) ማንኛውም ድርጅት ከምርቱ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት በምግብ ንክኪ ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡
2) ሠራተኞች ስራ ከመጀመራቸውም ሆነ በስራ ላይ እያሉ ስለ መሠረታዊ አዮዲን ያለው ጨው አከመቻቸት፣ ባህሪያት፣ አያያዝና መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ እና የመሳሰሉ ስልጠናዎች መውሰድ አለባቸው፡፡

3) ድርጅቱ በምግብ ጨው ማምረት ወይም ሽያጭ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች በየ ስድስት ወሩ የተላላፊ በሽታ ምርመራ እንዲያካሂዱ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

4) ማንኛውም በምግብ ጨው ማምረት ወይም ሽያጭ ስራ ላይ የተሰማራ ሰራተኛ በስራ ጊዜ በማንኛውም ተላላፊ በሽታዎች ታሞ የበሽታ ምልክቶችን እንደ ተቅማጥ፣ ትኩሳት፣ ትውከትና የመሳሰሉት ካለበት በሽታው እስኪድን ድረስ ከዚሁ ስራ ታግዶ መቆየት አለበት፡፡

5) የሰራተኞች የግል ንጽህና አጠባበቅ በየጊዜው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

6) የድርጅቱ ሰራተኞች እንደየ ስራው ባህሪ የስራ ደህንነት መከላከያ መሳሪያዎች ሊያደርጉ ይገባል፡፡

7) ሠራተኞቹ በድርጅቱ ውስጥ ሊያጋጥሙ ስለ ሚችሉ አደጋዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችና አሰራሮች እንደ እሳት አደጋ ማጥፊያ፤ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ በቂ ስልጠና መውሰድ አለባቸው፡፡

## 17. የቴክኒካል ባለሞያ ሃላፊነት

1) ማንኛዉም ቴክኒክ ባለሞያ በድርጅቱ ውስጥ ከምግብ ጨው ደህንነትና ጥራት መጓደል ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ማንኛውም የጤና ችግሮች ከድርጅቱ በተጨማሪ ባለሙያውም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም ሰራተኛ በአካሉ ላይ ጉዳት ከደረሰበት ወይም በእጁ ላይ ቁስል ካለው ቁስሉን መሸፈንና እስኪድን ድረስ ከምግብ ጨው ጋር ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት ማቆም አለበት፡፡

3) የቴክነክ ባለሞያው የስራ ግዴታውን ለመወጣት የማይችል የአእምሮ ሕመም ያለበት ወይም የአልኮል መጠጥ፣ የናርኮቲክና የሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ወይም ሌሎች አደንዛዥ እፆች ሱሰኛ መሆን የለበትም፡፡

4) የቴክኒክ ባለሞያው በተለያየ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ በስራው ላይ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ሊሰራ የሚችል ተመሳሳይ ሞያ ያለው ባለሞያ መኖር አለበት፡፡

5) የቴክኒክ ባለሙያዉ በድርጅቱ የተመረተ የምግብ ጨው ጥራት ጉድለት ወይም የተቀመጠውን ደረጃ የማያሟላ መሆኑን ሲያዉቅ ወይም ሲሰማ ሁኔታዉን ለድርጅቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

6) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ የሚቀርብለትን መረጃ በጊዜው የማያስተካክልና ተደጋጋሚ ጥፋቶች ሲፈፅም ባለሞያው ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

7) ማንኛውም ድርጅት ስለ እያንዳንዱ ባለሙያ የስራ ድርሻና ኃላፊነት የሚገልጽ ሰነድ ማዘጋጀትና ሁሉም ባለሙያዎች ስለምርቱ አያያዝና አጠባበቅ ስልጠናዎች እንዲወስዱ ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የምግብ ጨው ስለ ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክና ጅምላ ማከፋፈል

### 18. የምግብ ጨው ስለማምረት

1) ማንኛውም ድርጅት ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው ማምረት የሚችለው ተፈላጊውን የአዮዲን መጠን ያለውን ጨው ብቻ ነው፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት ጨውን ማምረትና በአዮዲን እንዲበለፅግ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች ይህንን ተግባር ለማከናወን ዓላማ ተብለው የተሰሩና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው፡፡
3) ማንኛውም በአዮዲን ለማበልፀግ የሚውል ጨው ቢያንስ 97% የሶድየም ክሎራይድ (NaCl) ውሁድ መጠን ሊኖረው ይገባል፡፡
4) ማንኛውም ለምግብነት የሚውል የምግብ ጨው የእርጥበት መጠን (Moisture content) ከ 3% መብለጥ የለበትም፡፡
5) ማንኛውም የምግብ ጨው የድቀት መጠን (Particle size) ከጠቅላላ ጨው ከ95% በላይ በአራት ሚሊሜትር የወንፊት ቀዳዳ (sieve size) ማለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

### 19. ስለ ጨው ማበልፀጊያ ውህዶች

1) ማንኛውም ድርጅት ጨውን በአዮዲን ማበልፀግ የሚችለው በፖታሽየም አዮዴት፣ ፖታሽየም አዮዳይድ፣ ሶድየም አዮዴት ወይም ሶድየም አዮዳይድ ውህዶችን በመጠቀም ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተዘረዘሩት ውህዶች በባለስልጣኑ ተመዝግበው በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የተመረቱና ጥራታቸው የተረጋገጠ መሆን አለባቸው፡፡

## 20. ስለ የአዮዲን መጠንና በካይ ነገሮች

1) ማንኛውም ድርጅት ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው ማቅረብ የሚችለው በአንድ ኪሎግራም የምግብ ጨው ውስጥ ከ34—66 ሚሊግራም ፖታሽየም አዮዴት ያለውን ጨው መሆን አለበት፡፡
2) በማንኛውም የምግብ ጨው ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ በካይ ነገሮች መጠን በሀገራዊ የመብል ጨው ደረጃ ላይ ከተቀመጠው መጠን ማለፍ የለባቸውም፡፡
3) በምግብ ጨው ላይ የሚጨመሩ እንደ የፀረ ግግር፣ ፀረ አረፋ፣ ፀረ ሞልድና ሌሎች በጨዉ ላይ የሚጨመሩ ኬሚካሎች በሀገራዊ የመብል ጨው ደረጃ ላይ የተቀመጠው መስፈርት መሟላት አለባቸው፡፡

## 21. የምግብ ጨው ስለ ማሸግ

1) ማንኛውም የምግብ ጨው ማሸግ የሚችለው የምግብ ጨው አምራች ድርጅት ብቻ ነው፡፡
2) ማንኛውም የምግብ ጨው ማሸጊያ በውስጡ ያለው የአዮዲን መጠንን ሳይባክን ሊያቆይ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
3) ለምግብ ጨው ማሸጊያ የሚውል ከረጢት እርጥበት ወይም ውኃ የማያስገባ፣ ከቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃንና ውጫዊ አየር የሚከላከልና በጨዉ ጥራት ላይ ተፅእኖ የማያሳድር ሆኖ ከሚከተሉት ማቴሪያሎች በአንዱ የተሰራ መሆን አለበት፤
   ሀ) ከፍተኛ ዝፈት ካለው ፖሊኢትሊን (HDPE) ፣
   ለ) ፖሊፕሮፒሊን (PP) የተሸፈነ ከረጢት ወይም
   ሐ) ኤል ዲ ፒ ኢ ጠርዝ ያላቸው ቃጫ ከረጢቶች (LDPE) ወይም ሌላ በባለስልጣኑ ተቀባይነት ካገኙ ግብአቶች፤
4) እንደ ማዳበሪያ፣ ሲሚንቶ ወይም ሌላ ኬሚካል ይዞ የነበረ ወይም ቀድሞ ጥቅም ላይ የዋለ ከረጢት ለምግብ ጨው ማሸጊያነት ማዋል አይችልም፡፡

## 22. ስለ ገላጭ ፅሁፍ

1) በማንኛዉም ምግብ ጨው ማሸጊያ ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚታተም ገላጭ ፅሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተጻፈ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ) የጨዉ ንግድ ስም፣

ለ) "የምግብ ጨው" የሚል ገላጭ ፅሁፍ፣

ሐ) በጨው ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን በሚግ/ኪግ ወይም ግ/ኪግ፣

መ) የጨው የተጣራ ክብደት፣

ሠ) የምርት መለያ ቁጥር (Batch Number) ፣

ረ) ጨው የተመረተበትና አገልግሎት የሚያበቃበት ጊዜ፣

ሰ) የአምራች ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ እና

ሸ) ጨው በቀዝቃዛ፣ ንፁህ፣ ደረቅና ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን በማይደርስበት ስፍራ ላይ መቀመጥ እንዳለበት የሚገልፅ ገላጭ ፅሁፍ፤

2) ማንኛውም ሰው አዮዲን ባለው ጨው ማሸጊያ ላይ በጉልህ የማይታይ ፅሁፍ፣ በቀላሉ ሊጠፉ የሚችል ወይም ሌላ አሳሳች ገላጭ ፅሁፍ መጠቀም ወይም መለጠፍ የተከለከለ ነው፡፡

3) በእያንዳንዱ በአገር ውስጥ የሚመረተው የምግብ ጨው ማሸጊያ ላይ ሀገራዊ የአዮዳይዜሽን አርማ ምልክት መኖር አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ስር የተጠቀሰው ምልክት የሚከተለው ይሆናል፤




## 23. የምግብ ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ሰለማስገባት

1) ማንኛውም ሰው ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው አዮዲን ያለው ጨው ሆኖ በዚህ መመሪያ የተቀመጡት አግባብ ያላቸው መስፈርቶችን ሲያሟላ ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም ሰው የምግብ ጨው ከመውጫና መግቢያ በር ላይ ለማስለቀቅ የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

   ሀ) ከኦርጅናሉ ጋር የተገናዘበ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ኮፒ፣

   ለ) የጤና ሰርተፊኬት (Health Certeficate) ፣

   ሐ) የምግብ ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት (Certificate of Analysis)፣

   መ) የስሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (Certeficate of Origin)፣

   ሠ) የምርት ሽያጭ ሰርተፊኬት (Free Sales Certeficate)

   ረ) የእቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ (Packing List)፣

   ሰ) የግምሩክ ዲክላራስዮን (Custom Diclaration)፣

   ሸ) ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል (Bill of Loading or Airway Bill)፣

   ቀ) ኢንቮይስ (Comercial Invoice)፣

## 24. የምግብ ጨው ወደ ውጭ ሀገር ስለ መላክ

ማንኛውም ሰው ጨው ወደ ውጭ ሀገር መላክ ሲፈልግ ለሚልከው ጨው የጤና ሰርተፊኬትና ሌሎች መረጃዎች እንዲሰጠው ሲጠይቅ ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላቱ ሲያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 25. የምግብ ጨው ስለ ማከፋፈል

1) ማንኛውም ሰው ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው ማከፋፈል የሚችለው በጨዉ ውስጥ ተፈላጊውን የአዮዲን መጠን ያለውን ብቻ ነው፡፡

2) ማንኛውም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የምግብ ጨው መግዛት የሚችለው ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠው የጨው አምራች ወይም አስመጪ ድርጅት ብቻ ነው፡፡

3) ማንኛውም ድርጅት የምግብ ጨዉ ሲገዛና ሲሸጥ የድርጅቱ ስምና ህጋዊ ማህተም ያረፈበት ደረሰኝ እንደቅደም ተከተሉ የመቀበልና የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 26. የምግብ ጨው ስለ ማከማቸት

1) ማንኛውም ድርጅት የምግብ ጨው ሲያከማች የጥራት ጉድለትና የአዮዲን ብክነት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች እንደ እርጥበትና ለቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን በተጋለጠ መልኩ ማከማቸት የለበትም፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት የምግብ ጨው ሲያከማች ከማከማቻ ክፍሉ ጣሪያ 50 ሴንቲሜትር ዝቅ ብሎ እና ከግድግዳው 20 ሴንቲሜትር ርቆ ማከማቸት አለበት፡፡
3) ድርጅቱ በማከማቻው ውስጥ ቀድሞ የተመረተ ወይም የገባ ጨው ቀድሞ ለማውጣት በሚያመች መልኩ መከማቸት አለበት፡፡
4) ድርጅቱ እንደየአከባቢው ሁኔታ የማከማቻ ክፍሉ ሙቀትና እርጥበት በየጊዜው በመለካት ከሚፈለገው መጠን በላይ ሲሆን አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ አለበት፡፡
5) ማንኛውም የተበላሸ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜዉ ያለፈበት የምግብ ጨው በአግባቡ ተቆጥሮና ተመዝግቦ ጥቅም ላይ ከሚውለው የምግብ ጨው ተለይቶ ለብቻው መቀመጥ አለበት፡፡
6) ማንኛውም ድርጅት በማንኛውም ሁኔታ የምግብ ጨው አዮዲን ከሌለው ጨው ቀላቅሎ ማከማቸት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ አይችልም፡፡

## 27. የምግብ ጨው ስለ ማጓጓዝ

ማንኛውም የምግብ ጨውን ሊበክልና በውሰጡ ያለውን የአዮዲን መጠን ሊያባክን ከሚችል እንደ ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን፣ ዝናብ፣ አቧራና ሌሎች በጨዉ ደህንነትና ጥራት ላይ ተፅእኖ ሊያሳደሩ ለሚችሉ ነገሮች በተጋለጠ መልኩ መጓጓዝ የለበትም፡፡

## 28. አዮዲን የሌለው ጨው በጥቅም ላይ ስለማዋል

1) ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር አዮዲን የሌለው ጨው በሀገሪቱ ውስጥ መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት አዮዲን የሌለው ጨው በጥቅም ላይ ሊያውል የሚችለው ለኢንዱስትሪ ግብአት፣ ለምርምር ወይም ሌላ ከሰው ምግብነት አገልግሎት ውጪ ለሆነ ዓላማ ሆኖ የሚያስፈልገው የጨው መጠን ለባለስልጣኑ አቅርቦ ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡
3) ማንኛውም ድርጅት ጨዉ ከሚመረትበት ቦታ ውጪ በሌላ ቦታ ወስዶ አዮዳይዜድ ለማድረግ ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

4) ማንኛውም ሰው አዮዲን የሌለው ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከባለስልጣኑ ልዩ የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

5) ማንኛውም ድርጅት የሚያመርተው ጨው አዮዲን የሌለው ከሆነ *"ለሰው ምግብነት አይውልም"* ወይም *"ለ____አገልግሎት ብቻ"* የሚል በጉልህ የተፃፈ ገላጭ ፅሑፍ በማሸጊያው ላይ መግለፅ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## አስተዳዳራዊ እርምጃዎች

### 29. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት

1) ማንኛውም ድርጅት የፈፀመው ጥፋት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ካልሆነ በስተቀር ባለስልጣኑ እንደአግባብነቱ የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2) ባለስልጣኑ ድርጅቱ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት አስፈላጊውን ማስተካከያ ካላደረገ ድርጅቱ ሊታገድ ይችላል፡፡

### 30. ስለ እገዳ

1) ማንኛዉም ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ ከ 1 ወር እስከ 6 ወራት ለሚደርስ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊያግድበት ይችላል፤

ሀ) ሕጋዊና ወቅታዊ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሌለው ድርጅት የምግብ ጨው ከገዛ ወይም በማንኛውም መንገድ ከተቀበለ ወይም ፈቃድ ለሌለው አከፋፋይ ድርጅት ከሸጠ፤

ለ) ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ በተቋሙ የቦታ አድራሻ ላይ ለዉጥ ካደረገ፣

ሐ) ከተጠቀሰው ቴክኒክ ባለሙያ እውቅና ውጪ የምግብ ጨው ሲያመርት፣ ሲያስመጣ፣ ሲልክ፣ ሲያከፋፍል ወይም ሲሸጥ፣

መ) በአእምሮ ሕመም ወይም ስራውን ለማከናወን በማያስችል የአካል ጉድለት ወይም የአልኮል መጠጥ፣ አደንዛዥ እፆች፣ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ሌላ በመውሰድ በሚነሳ የአእምሮ ህውከት ምክንያት ወይም በዕድሜ መግፋት ምክንያት ተግባሩን በአግባቡ ማካሄድ የማይችል ባለሞያ ሲያሰራ፤

ሠ) እንደአከባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለውን አዮዲን ከብክነት ለመከላከል የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንድሽነር ሳይኖረው ጨው ሲያመርት፣ ሲያከማች ወይም ሲያጓጓዝ፤

ሸ) ባለሥልጣኑ በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው ማንኛውም የኢንስፔክሽን ስራዎች እንዳያከናውን እንቅፋት የፈጠረ እንደሆነ፣

ቀ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ (7) ስር ከተጠቀሱት መስፈርቶች መካከል አንዱን ሲያጓድል፤

በ) ድርጅቱ ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ጉድለቱን የማያስተካክል ከሆነ ወይም

ተ) ከነዚህ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ጥፋቶችን ፈፅሞ ሲገኝና የበላይ ሃላፊ ሲያፀድቃቸው፤

2) ማንኛውም ድርጅት አግባብ ባለው አካል በንግድ ሥራ ላይ እንዳይቀጥል ከታገደና፤

## 31. ስለ ስረዛ

1) ማንኛዉም ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ ቢያንስ ለ1 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተገኘው በማጭበርበር መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ፣

ሐ) ማንኛውንም የምግብ ጨው መጀመሪያ በአምራቹ ድርጅት ከተሰራ ወይም ከነበረው የሚዛን ክብደት ለመጨመር፣ መልክ ለማሳመር፣ ወይም ለሌላ ተግባር ባዕድ ነገር ጨምሮ ሲገኝ፣፤

መ) የተበላሸ፣ የአገልግሎት ዘመን ያለፈበት፣ ገበያ ላይ እንዳይዉል የታገደ፣ አዮዲን የሌለው፣ ስለምርቱ ሁኔታ ገላጭ ጽሁፍ የሌለዉ ወይም አሳሳች ገላጭ ጽሁፍ ያለው የምግብ ጨው የያዘ፣ የሸጠ ወይም ያከፋፈለ ወይም የምግብ ጨው የከለሰ፣ አመሳስሎ ያቀረበ ፣ በህገወጥ መንገድ የምግብ ጨው የያዘ ወይም ይህንን ስራ መከናወኑን አውቆ የምግብ ጨዉን ከያዘ፣ ከሸጠ ወይም ካከፋፈለ፤

ሠ) የማምረት ፈቃድ ሳይኖረው የምግብ ጨው እንደገና ያሸገ ወይም ሌላ ገላጭ ፅሁፍ በመለጠፍ ከሸጠ፣

ሸ) በአንቀጽ (11) መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በወቅቱ ካልታደሰ፣

ቀ) ድርጅቱ ስለ እገዳ የተመለከተውን በአንቀፅ (30) ላይ የተቀመጡትን ተመሳሳይ ጥፋቶች ከሁለት ጊዜ በላይ ፈፅሞ ሲገኝ ወይም ድርጅቱ በባለስልጣኑ የተጣለበትን እገዳ በመተላለፍ ስራውን ከቀጠለ፤

በ) ከህብረተሰብ ጤና ቁጥጥር አንጻር ባለስልጣኑ አስፈላጊ እና ምክንያታዊ ነው ብሎ ያመነባቸዉንና የበላይ ሀላፊ ያጸደቃቸዉ ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶች ሲፈፅም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊሰርዝበት ይችላል፡፡፤

2) አግባብ ባለው አካል ድርጅቱ በንግድ ሥራ እንዳይቀጥል ፈቃዱ ሲሰረዝ ወይም የንግድ ስራውን በራሱ ፈቃድ ሲያቋርጥ፡፡

## 32. የምግብ ጨውን ሰለ መያዝ

1) ባለ ስልጣኑ ማንኛውም የምግብ ጨዉን ጥራትና ደህንነት ጉድለት መኖሩን ጥርጣሬ ሲኖረው ወይም በህብረተሰቡ ጤና ላይ አደጋ ሊያደርስ ይችላል ብሎ ሲያምን የምግብ ጨዉን ጥራትና ደህንነት እስኪረጋገጥ ድረስ ለብቻው ተገልሎ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ተገልሎ የተያዘ የምግብ ጨው አስፈላጊውን ምርመራ ተደርጎበት የምግብ ጨዉ በጥቅም ላይ የማይውል መሆኑ ከተረጋገጠ ተይዞ ሊወገድ ወይም ወደ መጣበት ሀገር ሊመለስ ይችላል፡፡

## 33. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ መመለስ

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ዓይነት፣ የቦታ ለውጥ ሲያደርግና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ መመለስ አለበት፡፡
2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ፣ ከታገደ፣ በተቀመጠው የእድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስ ከቀረ ወይም በራሱ ፈቃድ ስራውን ካቋረጠ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ መመለስ አለበት፡፡

## 34. እገዳና ስረዛ ስለማንሳት

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ድርጅት የተጣለበት እገዳ ወይም ስረዛ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ለእገዳ ወይም ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲያጠናቅቅ ባለስልጣኑ እገዳው ወይም ስረዛው ሊያነሳለት ይችላል፡፡

## 35. የምግብ ጨው ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ

ማንኛውም ስራውን በራሱ ፈቃድ ያቋረጠ፣ እገዳ ወይም ስረዛ የተጣለበት ድርጅት በእጁ የሚገኘውን ጥቅም ላይ መዋል የሚችል የምግብ ጨው በባለስልጣኑ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላላቸው ሌሎች ድርጅቶች ማስተላለፍ ይችላል፡፡

## 36. የምግብ ጨው ከገበያ ላይ ስለ መሰብሰብ /Product recall/

1) ማንኛውም ድርጅት ያመረተው ወይም ያሰራጨውን የምግብ ጨው ጥራት ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ጠቋሚ ነገሮች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ማንኛውም ዓይነት ሽያጭ እንዳይከናወን የማሳወቅና የማስቆም ግዴታ አለበት፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት ያመረተውን፣ ያስመጣውን፣ የላከውን ወይም ያከፋፈለውን የምግብ ጨው የጥራትና ደህንነት ጉድለት ኖሮት ለህብረተሰቡ ጤና ጎጂ መሆኑ ሲረጋገጥ ከገበያ የመሰብሰብና ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

3) ድርጅቱ በምግብ ጨዉ ብልሽት ምክንያት በህብረተሰብ ጤና ላይ ለደረሰ ችግር አግባብ ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 37. የተበላሸ ወይም ተፈላጊውን ደረጃ ስለ ማያሟላ የምግብ ጨው

1) ማንኛውም ድርጅት በተለያዩ ምክንያቶች የተበላሸ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበትና ተፈላጊውን ደረጃ የማያሟላ የምግብ ጨው ለይቶ የመያዝና ዝርዝራቸውን ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
2) በምግብ ጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን የተቀመጠውን ደረጃ የማያሟላ ከሆነ ድርጅቱ አስፈላጊው አስተዳዳራዊ እርምጃ ተወስዶበት ጨዉን በባለስልጣኑ ፈቃድ እንደአግባቡ ተመልሶ በድጋሚ በአዮዲን እንዲበለፅግ ሊደረግ፣ ሊወገድ ወይም ከሰው ምግብነት ውጪ ዓላማ ሊውል ይችላል፡፡
3) የምግብ ጨዉ በተለያየ ምክንያት ለሰው ጤና ጎጂ በሆኑ እንደ ፀረ ተባይና በሌሎች አደገኛ ኬሚካሎች የተበከለ ከሆነ መወገድ አለበት፡፡
4) የምግብ ጨዉ እንዲወገድ የሚደረግ ከሆነ በባለስልጣኑ የምግብ ማስወገድ መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 38. አስተዳዳራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ

1) በዚህ ክፍል መሰረት የሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች በባለስልጣኑ የአስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
2) ማንኛዉም ድርጅት ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ እድሳት፣ እገዳና ስረዛ ወይም ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸዉ እርምጃዎችን በተመለከተ ቅር ከተሰኘ አቤቱታውን በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ባለስልጣኑ ላቋቋመዉ ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡
3) ቅሬታ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን አጣርቶ በ30 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 39. መረጃ ስለ መያዝ

1) ማንኛዉም ድርጅት ስለ አስመጣው፣ ስለ አከፋፈለው፣ ስለ ላካዉ፣ ስለተበላሸ፣ የመጠቀሚያ ጊዜዉ ስለአለፈበት፣ ስለተወገደ ጨውና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ሰነዶችን በአግባቡ የመያዝና በባለስልጣኑ ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

2) በድርጅቱ ውስጥ ስላለው ሰራተኛ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ፣ የጤና ሁኔታና የወሰዱት ስልጠና ዓይነት የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ የያዘ ፋይል መኖር አለበት፡፡

3) ድርጅቱ ዝርዝር ኢንቮይሶች፣ ደረሰኞች፣ የክምችት መቆጣጠሪያ ስቶክና ቢን ካርዶችና ሌሎች መረጃዎች ሊኖረው ይገባል፡፡

4) ድርጅቱ ጨዉን የገዛበትና የሸጠለትን ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ የሚገልፅ መረጃ መያዝ አለበት፣

5) ማንኛዉንም ድርጅት ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎችን በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

### 40. የምግብ ጨው ስለ ማስተወወቅ

ማንኛዉም ድርጅት በማንኛውም የማስታወቂያ መንገድ ተጠቅሞ የምግብ ጨውን ማስተዋወቅ የሚችለው አግባብ ባለው የማስታወቂያ ህግ መሰረት ይሆናል፡፡

### 41. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ

1) ባለሥልጣኑ የወሰደውን ማንኛውም አስተዳዳራዊ እርምጃ በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ወይም ቅሬታ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ መረጃዎቹን ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) ባለሥልጣኑ በማንኛውም ድርጅት ያገኛቸው የአሰራር ግድፈቶች፣ የተረጋገጡ ተጨባጭ ጥቆማዎች ሲያገኝና መረጃው ለሕብረተሰቡ ባለመነገሩ በህብረተሰቡ ጤና ላይ አደጋ

ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ሲታመን መረጃዎቹ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ይፋ ሊያደርግ ይችላል።

3) ማንኛውም ድርጅት የድርጅቱን ስምና አድራሻ የሚገልፅ ሊነበብ በሚችል ጉልህ ፊደል ቢያንስ በአማርኛ ቋንቋ ፅፎ ድርጅቱን ሊያመላክት በሚችል ቦታ ላይ ማኖር አለበት፡፡

4) ማንኛዉም ሰዉ በባለሥልጣኑ ምስጢር ተብለው ከተያዙ መረጃዎች በስተቀር ስለ ማንኛውም ድርጅት የሚፈልገውን መረጃ ማግኘት ይችላል።

## 42. ስለ አግልግሎት ክፍያ

ማንኛዉም ድርጅት በባለስልጣኑ ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብ ባለው አካል በሚወስነው በሚወሰነው የክፍያ ተመን መሰረት መክፈል ይኖርበታል፡፡

## 43. የመተባበር ግዴታ

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 44. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ዓይነት መመሪያ፣ የአሰራር ልምድ ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ በዚህ መመሪያ ላይ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 45. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

የሁሉ ደነቀው

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለልጣን
Ethiopian Food, Medicine and Health Care Adminstration and Control Authority

**<u>እዝል 1</u>**

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
## <u>መጠየቂያ ቅጽ</u>

1. የአመልካች ሙሉ ስም ___________________________
2. አመልካቹ/ቿ በድርጅቱ ያለው ኃላፊነት_____________________________________
3. የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም______________________________________________
   አድራሻ

   ክልል__________ዞን/ክ/ከተማ___________ወረዳ___________ከተማ_________ቀበሌ______________ስ/ቁ ____________ ሞ/ቁ_____________ኢሜይል__________________________________

4. የድርጅቱ አድራሻ

   ክልል ___________ ዞን/ክ/ከተማ___________ወረዳ_____________ከተማ_________________
   ቀበሌ___________________ስ/ቁ_______________ሞ/ቁ____________ኢሜል_______________
   የቦታው ልዩ መጠሪያ_________________________________________________________________

5. የድርጅቱ ዓይነት

   ☐ አምራች ☐ አስመጭ ☐ ጅምላ አከፋፋይ ☐ ላኪ

6. የሚይዘው የምግብ ዓይነት ______________________________________________________
   _____________________________________________________________________________

7. የድርጅቱን የቴክኒክ ባለሙያ
   7.1 ሙሉ ስም ______________________________
   7.2 የትምህርት ደረጃ ___________________________
   (የባለሞያው የውል ስምምነትና የትምህርት ማስረጃ ይያያዝ)
8. እኔ ___________________________ የተባልኩኝ በምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች ስላሟላሁኝ ድርጅቱ ታይቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡፡

   ፊርማ ____________________________

   ቀን __________________________

---

9. **ለቢሮ ስራ ብቻ የሚያገለግል**

   - ማመልከቻውን የተቀበለው ሰራተኛ ስም __________________________ፊርማ __________
   - ማመልከቻውን የተቀበለበት ቀን ____________ሰዓት___________________
   - የቀጠሮ ቀን ________________ሰዓት_____________

የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

Ethiopian Food, Medicine and Healthcare Adminstration and Control Authority

<u>እዝል 2</u>

## በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን ለማሟላት ከድርጅቱ ጋር የሚገባ መተማመኛ ሰነድ

1. የድርጅቱ ስም ______________________________የምርት ዓይነት ________________________
2. ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ ክልል ____________ ዞን/ክፍለከተማ _________ ወረዳ _________ ከተማ _____________ ቀበሌ ___________ ልዩ መጠሪያ ______________ ስልክ ቁጥር __________
3. የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ _________________________________

| ተ ቁ | በድርጅቱ ውስጥ የተገኙ ክፍተቶች | በድርጅቱ መወሰድ ያለባቸው የማስተካካያ እርምጃዎች | የጊዜ ወሰን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

| የኢንስፔክተሩ ስም ፊርማ | የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ ስም ፊርማ |
|---|---|
| 1. _________________ _________<br>2. _________________ ________<br>3. _________________ ________<br>ቀን ______________________________ | ______________________ ________<br><br>ቀን ______________________________ |

***<u>ማሳሰቢያ</u>***

- *ድርጅቱ የተቀመጠውን መስፈርት ከ 60 ፐርሰንት በላይ አሟልቶ ፍቃድ የሚሰጠው ከሆነ ጉድለቶችን ለማስተካከል ይህ የመተማመኛ ቅፅ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለድርጅቱ የሚሰጥ 2ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር ይያዛል፣3ኛ ኮፒ ሊአንስፔክሽንና ሰረቬላንስ ዳይሬክቶሬት ለክትትል ይሰጣል።*
- *ድርጅቱ መስፈርቱን ሳያሟላ ቀርቶ በድጋሚ ፈቃድ ለማውጣት የሚመለስ ከሆነ ይህ የመተማመኛ ቅፅ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ 1ኛ ኮፒ ለድርጅቱ የሚሰጥ 2ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር ይያያዛል።*
- *ድርጅቱ በገባው የመተማመኛ ሰነድ መሰረት ክፍተቶቹን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ካላሟላ አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስተዳዳራዊ እርምጃ ይወሰድበታል።*

photo

# የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
# Ethiopian Food, Medicine & Health Care Administration & Control Authority

## የምግብ ጨው ማምረቻ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
## Certificate of Competence For Iodizes salt Manufacturing Organization

ቁጥር /No ________________
ቀን /date__________________

የድርጅቱ ስም ____________________ የንግድ ስራ ዓይነት______________________________
Name of business organization Buisness type
የሚያመርተው የምርት ዓይነት ____________________________________________________________
Product Type

የድርጅቱ አድራሻ
Address of the organization
ክልል ___________________ዞን/ክ/ከተማ ________________ወረዳ ___________ከተማ _____________
Region Sub city/Zone Woreda City
ቀበሌ ______________ የቤ/ቁጥር___________ስ/ቁጥር ___________________ፋክስ______________
Kebele House no Telephone Fax

የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም _____________________________________
Owners Full Name

ድርጅቱ ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርቶች ማሟላቱ ስለተረጋገጠ በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አሰተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 መሰረት ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

This Certificate of Competence is issued upon fulfillment of requirements set by the Authority in accordance with Food, Medicine and Healthcare Administration and Control Proclamation No. 661/2009.

__________________________ ______________________
የኃላፊ ፊርማ የተሰጠበት ቀን
Signature of Authorized Person Date of Issue

| | | |
|---|---|---|
| ታድሳል<br>Renewed<br>200___ E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature | ታድሳል<br>Renewed<br>200___ E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature | ታድሳል<br>Renewed<br>200___ E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature |

ማሳሰቢያ /Notice/

ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
This certificate of competence

1. በየአመቱ ካልታደሰ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡
   Shall be considered cancelled unless renewed every year.
2. ድርጅቱ አግባብ ካላቸው ህጎችና መስፈርቶች ውጭ ሲሰራ ሲገኝ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
   may be suspended or revoked if the organization is found in violation of applicable laws & standards.
   Authority

Phot
o

የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
Ethiopian Food, Medicine & Health Care Administration & Control Authority

# የምግብ ጨው ላኪ፣አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
# Certificate of Competence for iodized salt Export/Import/Wholesale Organization

ቁጥር /No. _______________
ቀን /Date _______________

የድርጅቱ ስም ____________________ የንግድ ስራ ዓይነት______________________________
Name of business organization Buisness type
የሚይዘው የምርት ዓይነት ______________________________________________________________
Product Type
የድርጅቱ አድራሻ
Address of the organization
ክልል ___________________ዞን/ክ/ከተማ ________________ወረዳ ___________ከተማ _____________
Region Sub city/Zone Woreda City
ቀበሌ _____________ የቤ/ቁጥር__________ስ/ቁጥር __________________ፋክስ______________
Kebele House no Telephone Fax

የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም ____________________________________
Owners Full Name

ድርጅቱ ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርቶች ማሟላቱ ስለተረጋገጠ በምግብ፣ የበድኃኒትና በጤና ክብካቤ አሰተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 መሰረት ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

This Certificate of Competence is issued upon fulfillment of requirements set by the Authority in accordance with Food, Medicine and Healthcare Administration and Control Proclamation No. 661/2009.

__________________________ _____________________
የሃላፊ ፊርማ የተሰጠበት ቀን
Signature of Authorized Person Date of Issue

| | | |
|---|---|---|
| ታድሳል<br>Renewed<br>200___ E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature | ታድሳል<br>Renewed<br>200___ E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature | ታድሳል<br>Renewed<br>200___ E.C/201___G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር _________<br>R/no<br>ፊርማ ____________<br>Signature |

ማሳሰቢያ /Notice/

ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
This certificate of competence

3. በየአመቱ ካልታደሰ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡
Shall be considered cancelled unless renewed every year.
4. ድርጅቱ አግባብ ካላቸው ህጎችና መስፈርቶች ውጭ ሲሰራ ሲገኝ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
may be suspended or revoked if the organization is found in violation of applicable laws & standards.

*አባል 3*

## አዮዲን የሌለው ጨው የግዢ ፈቃድ መጠየቂያና መስጫ

### I. በድርጅቱ የሚሞላ

1. የአመልካች ሙሉ ስም ______________________
2. አመልካቹ/ቿ በድርጅቱ የሚኖረዉ/ራት ኃላፊነት /መረጃ ይያያዝ/፣ ______________________
3. የድርጅቱ ስም ______________________________
4. የድርጅቱ አድራሻ፣
   ክልል ________ ዞን/ክ/ከተማ________ወረዳ_________ከተማ_________
   ቀበሌ_____________ስ/ቁ___________ሞ/ቁ_________
   የቦታው ልዩ መጠሪያ______________________________________________

11. ጨዉ የተፈለገበት ዓላማ ______________________________________
12. የማከማቻ መጋዘን አድራሻ ____________________________________

| የሚፈለገው የጨው መጠን (ኪግ/ኩንታል) | ጨዉ የሚገዛበት ቦታ/ሀገር | የጨዉ አምራች ድርጅት ስም | ጨዉ የሚገባበት መግቢያ በር | የማጓጓዣ ዓይነት | የሚጓጓዝበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

የአመልካቹ ስም ____________________ፊርማ _______ቀን _________ ማህተም

---

### II. በባለስልጣኑ የሚሞላ

ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ድርጅት ለ __________________ አገልግሎት የሚውል ________ኪግ/ኩንታል አዮዲን የሌለው ጨው ወደ ሀገርውስጥ እንዲያስገባ/ ከሀገር ውሰጥ እንዲገዛ፣ እንዲያጓጉዝና እንዲያከማች በባለስልጣኑ "የምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 5/2004" መሰረት የተፈቀደለት መሆኑን እየገለጽን ድርጅቱ እስከ …………………ባለው ቀን ውስጥ አጓጉዞ እንዲጨርስ እናሳስባለን፡፡

የፈቀደው ሀላፊ ስም ____________________ ፊርማ _________ቀን __________ ማህተም

#### *ማሳሰቢያ*

*ይህ የግዢ ፈቃድ*

1. *የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ጭነት ብቻ ሆኖ ከላይ ለተገለፀው የጨው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡*
2. *ጨዉ በሚገዛበት፣ በሚጓጓዝበትና በሚከማችበት ጊዜ መለየት የለበትም፡፡*
3. *በ 3 ኮፒ የሚዘጋጅ ሆኖ 1ኛ ኮፒ ለድርጅቱ፣ 2ኛ ኮፒ ለኢንስፔክሽንና ሰርቬላንስ ዳይሬክቶሬት የሚሰጥ ሆኖ 3ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር የሚያያዝ ነው፡፡*